# ለተጠቃሚዎች ጠቃሚ መረጃ

ይህንን ጠቃሚ መረጃ ስላነበቡ እናመሰግናለን። ጥያቄ ካለዎት የመስሪያ ቤታችን ባልደረቦችን መጠየቅ ይችላሉ። ምስጢርዎ እንደተጠበቀ ነው።

## የጉዳይዎ ተከታታይ ሹምና የህክምናዎ እቅድ

የጉዳይዎ ተከታታይ ሹም የእርስዎን ጉዳይ የሚከታተለው ቡድን አባል ነው። ሹሙ ከእርስዎ ጋር በመገናኘት በቅርብ ይሰራሉ ፤ የእርስዎ የአእምሮ ጤንነት ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት መደረግ የሚገባውን ድጋፍ ሁሉ ስለ መደረጉ ያረጋግጣሉ የሚያስፈልግዎት እንክብካቤ እንዲያገኙም ያስተባብራሉ ።

ከቤተሰብዎ፣ ከተንከባካቢዎ ወይም ከጠበቃዎ ጋር ስላሉበት ሁኔታና ስለሚፈልጉት እንክብካቤ እንደሚያወያዩት ሁሉ ከጉዳይዎ ተከታታይ ሹምም እንደዚሁ ይወያዩ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ለህክምና ሲመጡ የሰጡት የምርመራ መረጃ በቀጣይነት ለሚወጣው የህክምናዎ እቅድ ይረዳ ዘንድ በክሊኒኩ ተመዝግቦ ተቀምጦአል። የህክምናዎ እቅድ አስመልክቶ መጠየቅ የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ በነፃነት መጠየቅ ይችላሉ። በጤንነትዎ ላይ የተገኘ ማንኛውም ዓይነት ለውጥ ካለ ማሳወቅ ጠቃሚ ነው።

## መረጃ ስለመስጠት

የእርስዎን የግል መረጃ ወይም ስለሚደረግልዎ እንክብካቤ በተመለከተ፤

- እርስዎን በየጊዜው ለሚከታተሉት የግል ሃኪም፣
- በፈቃድዎ የግል መረጃ መስጫ ቅፅ ሲሞሉ፣
- በጣም አልፎ አልፎ የሚከሰት ቢሆንም በህግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ መረጃው ሊሰጥ ይችላል።

## የተጠቃሚዎች አስተያየት

በሽተኞችና ጎብኚዎች የታዘቡትን እንዲነግሩን በደስታ እንጠብቃለን። የተገልጋዮች የእርካታ ቅኝትና የቅሬታ ወይም የምስጋና ቅጾች ከዚህ የመረጃ ስብስብ ጋር አብረው ተያይዘዋል። የሚሰጡት የቅሬታ አስተያየት በምስጢር ይጠበቃል። እርስዎን በምንም ዓይነት መልኩ አይነካም። ምስጋናዎ ግን ለሰራተኞቹ ይነገርልዎታል።

የተሞሉ ፎርሞች NMAHS MH አገልግሎት ባለው ምስጢራዊ የተጠቃሚዎች የሃሳብ መስጫ ሳጥን ማስገባት ይቻላል። ስለሰጡት አስተያየት ምላሽ የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎትን አድራሻዎንና የስልክ ቁጥርዎን ያካትቱበት።

የጉዳይዎ ተከታታይ ሹም ያለብዎትን ችግር ለመፍታት ወይም ጥያቄዎን ለመመለስ ሁልጊዜ ዝግጁ መሆናቸውን ያስታውሱ። አድራሻቸውንና ስልክ ቁጥራቸውን ካርዳቸው ላይ ይመልከቱ ። እርስዎ ከህመምዎ ለመዳን በሚያደረጉት ጥረት ሁሉ አብረንዎት እንሰራለን።

በ Joondalup Consumers Group ሚያዝያ 2006 ተሻሽሎ የወጣ

(Amharic Translation)